የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ ጥር ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 11
ADDIS ABABA 21st January, 2020

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፷፩/፪ሺ፲፪ ዓ.ም
የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ……………………ገጽ ፲፪ሺ፺፪

## Content

Regulation No. 461/2020
Council of Ministers Commercial Registration and Licensing (Amendment) Regulation …. Page 12092

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፷፩/፪ሺ፲፪

### የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፪/፪ሺ፱ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፣

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፱፻፹/፪ሺ፲ አንቀጽ ፶፪(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክርቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፬፻፷፩/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ማሻሻያ**

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ደንብ ቁጥር ፫፻፺፪/፪ሺ፱ እንደሚከተለው ተሻሽሏል:-

፩/ የደንቡ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተተክቷል:-

"፬/ በንግድ ማኅበር የንግድ ስም እንዲሻሻል ሲጠየቅ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ ስለመሻሻሉ ለዚህ በተዘጋጀ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አውታርን በመጠቀም ያሳውቃል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 461/2020

### COMMERCIAL REGISTRATION AND LICENSING (AMENDMENT) REGULATION

**WHEREAS,** it has been found necessary to Amend, the commercial Registration and licensing service Regulation No 392/2016;

**NOWTHEREFORE,** the Council of Ministers has hereby issued this Regulation pursuant to Article 52 (1) of the Commercial Registration and Licensing Proclamation No. 980/2016.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Council of Ministers Commercial Registration and Licensing (Amendment) Regulation No. 461 /2020."

**2. Amendment**

Commercial Registration and Licensing Regulation No.392/2016 is hereby amended as follows:

1/ Sub Article (4) of Article 7 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Sub Article (4):

"4/ Where a request is made for an amendment of a company name of a business organization, authenticated minutes the relevant organ shall notify the amendment via information communication technology channels.

፪/ በደንቡ በየትኛውም ቦታ ላይ "አመልካቹ የዋና ሥራ አድራሻና የቅርንጫፍ የሥራ አድራሻ ያለው ከሆነም ይህንኑ የሚያረጋግጥ የአድራሻ ማረጋገጫ "የሚለው ተሰርዞ "አግባብ ያለው አካል በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የአመልካች የንግድ ሥራ አድራሻ" በሚል ተተክቷል፡፡

፫/ የደንቡ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ረ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ረ) ተተክቷል:-

"ረ/ አመልካቹ የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲሁም ቅርንጫፍ የሚከፍት ከሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያዘጋጀው የምዝገባ ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የንግድ ሥራ አድራሻ የአመልካቹ የንግድ ሥራ አድራሻው ነው ተብሎ ይወሰዳል፡"

፬/ የደንቡ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፡

"፪/ ግለሰብ ነጋዴ በውክልና የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀትን ለማውጣት ሲፈልግ ወኪሉ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ የውክልና ማስረጃ ሠነድ ማቅረብ አለበት፡"

፭/ የደንቡ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሠ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሠ) ተተክቷል:-

"ሠ) ለበጀት ዓመቱ ለደመወዝ እና ለሥራ ማስኪያጃ የሚሆን ቢያንስ ፩፻ሺ (አንድ መቶ ሺ) የአሜሪካን ዶላር ወደ አገር ውስጥ በወኪዩ ስም ወይም በእንደራሴው ስም ለማስገባቱ ከባንክ የተሰጠ ማረጋገጫ፡"

፮/ የደንቡ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተተክቷል:-

"፬/ ማሻሻያው የሚደረገው በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ከሆነ የማኅበሩ አባላት ማሻሻያ ያደረጉበትን ሠነድ ለማረጋገጥ በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ ዋና ቅጅ፡ ማሻሻያው ከካፒታል ጋር የሚያያዝ ከሆነ ወይም የአድራሻ ለውጥ ከሆነ ሠነድን ለማረጋገጥ

2/ The expression which provides "statement of principal business address of applicant and branch office, if any in any of the provisions in the Regulation is deleted and replaced by "the business address stated and signed by the applicant in the form prepared by the relevant body for this purpose."

3/ Paragraph (f) Sub Article (1) of Article 9 of the Regulation is deleted and replaced by the following new paragraph (f):

"f/ Where the applicant is a foreign national, in addition to those provided in this Article, he shall produce an investment license and the business address stated and signed in the form prepared for the purpose by the relevant body shall be taken as his business address."

4/ Sub Article (2) of Article 9 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Sub Article (2):

"2/ Where a commercial registration of a sole business is made via an agent through a power of attorney, a power of attorney authenticated by a legally authorized body shall be produced."

5/ Paragraph (e) Sub Article (1) of Article 13 of the Regulation is deleted and replaced by the following new paragraph (e):

"e/ a bank statement certifying deposit of a minimum of USD 100,000(One hundred thousand) earmarked for salary and administrative expenses is deposited in the name of the principal or in the name of his representative;"

6/ Sub Articles (4) of Article 18 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Sub Articles (4):

"4/ The business address stated and signed by the business organization in the form shall be taken as his business address , Where the amendment is to be made to the memorandum or Articles of association, an original copy of the minutes of shareholders decision to amend same, authenticated by a legally

በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የማኅበሩ ቃለ ጉባኤ ዋና ቅጅ እና የአድራሻ ማሻሻያ ቅፅ ላይ በመሙላት በፊርማው ያረጋገጠው በቅፁ የተመለከተው አድራሻ የንግድ ሥራ አድራሻው፡"

፯/ የደንቡ አንቀጽ ፳፩ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፩ ተተክቷል፡

"፳፩. <u>የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ</u>

፩/ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅፅ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

ሀ) የሥራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውና አስፈላጊ ገፆች ፎቶ ኮፒ፡

ለ) ማመልከቻው በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማስረጃ ዋና እና ፎቶ ኮፒ፣ የወኪሉና የሥራ አስኪያጁ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናው እና አስፈላጊ ገጾች ፎቶ ኮፒ፡

ሐ) የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ማስረጃ፡

መ) የንግድ ማኅበር ከሆነ የማኅበሩን ስረዛ ቃለ ጉባኤ (ዋናውን) እና የኦዲት ሪፖርት፡፡

፪/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት መሰረዙን ለዚህ ተግባር ያዘጋጀውን የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አውታር በመጠቀም ያሳውቃል፡፡"

፰/ የደንቡ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተክቷል:-

"፪/ ግለሰብ ነጋዴ የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀትን በውክልና ለማውጣት ተወካዩ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተረጋገጠ የውክልና ሥልጣን ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡"

፱/ የደንቡ አንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፮) ፊደል ተራ (መ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (መ) ተተክቷል:-

authorized body and where the amendment relates to capital or where it is change of business address, the original copy of minutes of the business organization authenticated by a legally authorized body;"

7/ Article 21 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Article 21:

"21. <u>Cancellation of Commercial Registration Certificate.</u>

1/ Application for cancellation of commercial registration certificate shall be submitted by attaching the following documents with the application form:

a) original and necessary copies of valid identity card or passport of the manager;

b) where the application is submitted by an attorney; original and copy of power of attorney, original and necessary copies of valid identity card or passport of the attorney and the manager;

c) certificate of commercial Registration;

d) in case of business organization, the minutes of cancellation resolution and audit report must be presented.

2/ the appropriate authority shall notify Cancellation of Commercial Registration Certificate via information communication technology channels."

8/ Sub Article (2) of Article 23 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Sub Article (2):

"2/ Where the license of a sole business is issued via a power of attorney, a power of attorney authenticated by an authorized body shall be produced."

9/ Paragraph (d) Sub Article (6) of Article 24 of the Regulation is deleted and replaced by the following new paragraph (d):

“መ/ የንግድ ማኅበሩ ቅርንጫፍ የሚከፍት ከሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያዘጋጀው ቅፅ ላይ በአመልካቹ የሚሞላ እና በፊርማው የሚረጋገጥ የንግድ ሥራ አድራሻው፡፡ ይህ አመልካቹ በቅፁ የተመለከተው አድራሻ ቅርንጫፍ የንግድ ሥራ አድራሻው ነው ተብሎ ይወሰዳል፡”

፲/ የደንቡ አንቀጽ ፴ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል:-

“፪/ የንግድ ማኅበር ከሆነ የኦዲት ሪፖርት፣”

፲፩/ የደንቡ አንቀጽ ፴፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል:-

“፫/ ማሻሻያው የሚደረገው በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ከሆነ የማኅበሩ አባላት ማሻሻያውን ያደረጉበት ሠነድን ለማረጋገጥ በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ ዋና ቅጅ፣ ማሻሻያው ከካፒታል ጋር የሚያያዝ ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ ወይም የአድራሻ ለውጥ ከሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያዘጋጀው ቅፅ ላይ ማኅበሩ የንግድ ሥራ አድራሻዬ ነው ብሎ የሞላው እና በፊርማው ያረጋገጠው የንግድ ሥራ አድራሻ የአመልካቹ የንግድ የሥራ አድራሻ ነው ተብሎ ይወሰዳል፡

፲፪/ የደንቡ አንቀጽ ፵፩ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፵፩ ተተክቷል፡

**፵፩. <u>የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ</u>**

፩/ የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማሰረዝ ከሚቀርብ ማመልከቻ ቅፅ ጋር የሚከተሉት መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

ሀ) የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ የምስክር ወረቀት፣

ለ) የሆሊዲንግ ስምምነት ስለመፍረሱ ሰነድ ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ፣

ሐ) የሆልዲንግ አስተባባሪ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውና አስፈላጊ ገጾች ፎቶኮፒ፡፡

“(d) Where the business organization ope branches, the business address stated a signed by it in the form shall be taken its business address;”

10/ Sub Article (2) of Article 30 of th Regulation is deleted and replaced by th following new Sub Article (2):

“2/ An audit report, if it is a busine organization;”

11/ Sub Article (3) of Article 32 of the Regulatio is deleted and replaced by the following ne Sub Article (3):

“3/ The business address stated and signed b the business organization in the form sha be taken as his business address , Whe the amendment is to be made to th memorandum or Articles of association, a original copy of the minutes shareholders decision to amend sam authenticated by a legally authorized bod and where the amendment relates to capit or where it is change of business addres the original copy of minutes of th business organization authenticated by legally authorized body.”

12/ Article 41 of the Regulation is deleted an replaced by the following new Article 41:

**“41. <u>Cancellation of the Special Certificat of Registration of Holding Company</u>**

1/ The holding company shall present th following, along with the applicatio to cancel special certificate c registration of holding company:

a) special certificate of registration o the holding company;

b) a notarized minute certificatio showing the dissolution of th holding company;

c) original and necessary copies o valid identification card or passpo of the manager of the holdin coordinator company.

፪/ የሆልዲንግ ስምምነቱ ስለመፍረሱ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ለዚህ ዓላማ ያዘጋጀውን የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አውታር በመጠቀም ይፋ ያደርጋል፡፡

፲፫/ የደንቡ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል:-

"፩/ በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ የፍራንቻይዘሩና የፍራንቻይዚ ውል ማፍረሻ ስምምነት ሰነድ፡"

፲፬/ የደንቡ አንቀጽ ፶፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል፡

"፫/ አምራቾች ወይም አስመጪዎች ከምርት ባህሪያቸው የተነሳ ለችርቻሮ ሽያጭ አስገዳጅነት ያላቸው ምርቶች በችርቻሮ ሊሸጡ ይችላሉ፡"

፲፭/ ከደንቡ አንቀጽ ፶፪ በኋላ አዲስ አንቀጽ ፶፫ ተጨምሮ ከአንቀጽ ፶፫ እስከ አንቀጽ ፶፭ ያሉት እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፶፬ እስከ አንቀጽ ፶፮ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"፶፫/ በዚህ ደንብ ስለመታወቂያ እና ፓስፖርት የተነገሩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የመንጃ ፈቃድ እና ከመሥሪያ ቤቶች የሚሰጡ መታወቂያዎችን በማቅረብም አገልግሎት ይሰጣል፡፡

**፫/ ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፪

ዶ/ር አብይ አህመድ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

2/ the appropriate authority shall notify Cancellation of the special certificate of registration of holding company via information communication technology channels."

13/ Sub-Article (1) of Article 51 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Sub Article (1):

"1/ a cancellation of the franchise agreement document approved by the appropriate authority;"

14/ Sub-Article (3) of Article 52 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (3):

"3/ Producers or importers may retail goods of such a nature that cannot be sold otherwise than by retailing;"

15/ New Article 53 is added After Article 52 and Article 53 to 55 shall be renumbered as Article 54 to 56:

"53/ Notwithstanding the provisions on identity card and passports under this Regulation, driving licenses and any identity cards issued by employers may be used for the purposes of getting any services."

**3. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 21st day of January,2020.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**